OFFICE OF ARTS & CULTURE
CITY OF SEATTLE

# አርቲስቶች በማዕከሉ (Artists at the Center) 2025-2026 መመሪያዎች

## የገንዘብ ድጎማው አጠቃላይ እይታ

አርቲስቶች በማዕከሉ (Artists at the Center)የሲያትል የስነ ጥበባት እና ባህል ጽሕፈት ቤት እና የሲያትል ማዕከልየብዙ ዓመታት ትብብር የሚያገኝ እና ከአፕታውን የስነ ጥበብ እና ባህል ጥምረት (Uptown Arts & Culture Coalition) እና በሲያትል ማዕከል ግቢ ዙሪያ በሚኖሩ ማህበረሰቦች የሚደገፍ ፕሮግራም ነው። ይህ ፕሮጀክት ከክላይሜት ፕሌጅ አሪና (Climate Pledge Arena) እና ሲያትል ክራከን (Seattle Kraken) በተገኘ ከ2021 ጀምሮ ለዘለቀ የ10-ዓመት የማህበረሰብ ጥቅም የገንዘብ ድጎማ መቋቋም ችሏል።

አርቲስቶች በማዕከሉ (Artists at the Center) በግላቸው የሚንቀሳቀሱ አርቲስቶች፣ የአርቲስት ጥምረቶች፣ የማኅበረሰብ ቡድኖች እና ድርጅቶች በሲያትል ማዕከል የተለያዩ የሥነ ጥበብ ዝግጅቶችን እንዲያቀርቡ ድጋፍ ያደርግላቸዋል። የሥነ ጥበብ ዘውጎች ሙዚቃን፣ ዳንስን፣ ቲያትርን፣ የሥነ ጥበብ ማሳያዎችን እና ብዙ የሙያ ዘርፎችን አካታች ያደርጉ ሥራዎችን ሊያካትቱ ይችላሉ። ብቅ-ባዮች በህዳር 2025 እና በመስከረም 2026 መካከል የጊዜ ሰሌዳ ተይዞላቸዋል። የተሸለሙ ተሳታፊዎች በአርቲስት/ቡድን መጠን እና የወሰን ውስብስብነት ላይ በመመስረት በገንዘብ $2,000፣ $4,000 ወይም $6,000 የገንዘብ ድጋፍ ያገኛሉ። በአሁኑ (2024-2025) ወቅት ላይ ተሸላሚ የሆኑ ተሳታፊዎች በመጪው የፕሮግራም ዓመት (2025-2026) ላይ ለማመልከት ብቁ አይደሉም።

ማመልከቻውን አስመልክቶ መረጃ እና እርዳታ ለማግኘት እባክዎ እነዚህን በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች ዝርዝር ይመልከቱ አልያም ደግሞ በበማዕከሉ የአርቲስቶች የፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ ሆነው የሚያገለግሉትን ዛክ ፍሪሜልን (Zach Frimmel) ወደ Zach.Frimmel@seattle.gov ኢሜይል በመጻፍ አልያም ደግሞ ወደ (206) 963-9226 በመደውል ማነጋገር ይችላሉ።

**የአሜሪካ የምልክት ቋንቋን (በቪድዮ በኩል) ጨምሮ እርስዎ በሚፈልጉት ቋንቋ ሊያነጋግሩዎ የሚችሉ አስተርጓሚዎች አሉን።**
እርስዎ ብቻ ደውለው የሚናገሩትን ቋንቋ ይንገሩን። ጥሪውን የሚቀላቀል አስተርጓሚ እስከምናገኝ ድረስ ለአፍታ ይጠብቁናል።

## ማመልከቻ

ማመልከቻዎን በሲያትል ከተማ የገንዘብ ድጎማ ድረ ገጽ በኩል በኦንላይን ማስገባት ይችላሉ፦https://seattle.fluxx.io/user_sessions/new

ኮምፒውተር ወይም የኢንተርኔት ተደራሽነት የሌለዎት ከሆነ ወይም ደግሞ ለማመልከት መሰናክል ሊሆንብዎት የሚችል ሌላ ማንኛውም ነገር ካለ የፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ የሆኑትን ዛክ ፍሬምልን (Zach Frimmel) ወደ (206) 963-9226 በመደወል ወይም ወደ Zach.Frimmel@seattle.gov ኢሜይል በመጻፍ ማነጋገር ይችላሉ። የተጠየቁትን ሁኔታዎች ለማቅረብ የፕሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ ከማመልከቻ ማብቅያ ቀኑ በፊት ቢያንስ ሁለት (2) ሳምንታት ያስፈልጓቸዋል።

## የሚያበቃበት ቀን

**ማክሰኞ፣ ሰኔ 17 ቀን 2025 ዓ.ም 5 ፒ.ኤም (ፓሲፊክ)**

ማመልከቻዎን ለመሙላት እና ለማስገባት የሚሆን በቂ ጊዜ እንዳለዎት ያረጋግጡ፤ ከ5 ፒ.ኤም (ፓሲፊክ) ማብቂያ ሰዓቱ በኋላ የሚገቡ ማመልከቻዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም።

## ብቁነት

ይህንን የገንዘብ ድጎማ ለማግኘት ብቁ ለመሆን የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርብዎታል፡-

- በሲያትል ከተማ በመደበኛነት ሥራዎን የሚያቀርቡ በግልዎ የሚንቀሳቀሱ አርቲስት፣ የአርቲስት ጥምረት፣ ድርጅት ወይም የማኅበረሰብ ቡድን መሆን።
- መገኛዎ ኪንግ ካውንቲ (King County) ውስጥ ወይም በዋሽንግተን ግዛት ውስጥ የሌላ ከተማ ባልሆነ የኪንግ ካውንቲ አካባቢ ላይ መሆን።
    - ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን፣ አካል ጉዳተኛ ሰዎችን፣ ስደተኛ እና ተፈናቃይ ማኅበረሰቦችን እና ከነጭ ማኅበረሰቡ ውጭ የሆኑ ማህበረሰቦችን ጨምሮ በሥርዓታዊ ጭቆና እጅግ የተጎዱ ማኅበረሰቦችን የሚወክሉ ድርጅቶች እና በግል የሚንቀሳቀሱ የሥነ-ጥበብ ባለሙያዎች እንዲያመለክቱ ይበረታታሉ።
- የፌዴራል የታክስ መታወቂያ ቁጥር (ሶሻል ሰኩሪቲ ነምበር ፣ አይቲን ወይም የሠራተኛ መለያ ቁጥር) ያለዎት እና በሲያትል ከተማ ውስጥ መሰረት ያደረጉ ወይም በአሁኑ ጊዜ ያለ በከተማው ፕሮግራሞችን እያካሄዱ ያሉ መሆን።
    - አመልካች ቡድኖች በ501(ሲ)(3) ሥር ለትርፍ ያልተቋቋሙ ቡድኖች መሆን ወይም ደግሞ ፊስካል ስፖንሰር ወይም ፊስካል ወኪል መጠቀም አይጠበቅባቸውም።
- ለዚህ ፕሮግራም ማስገባት የሚችሉት በማመልከቻ ጊዜ ዑደት አንድ ማመልከቻ ብቻ ነው።
- በርካታ አመልካቾች ለአንድ የሥነ ጥበብ ዝግጅት ማመልከቻ ማስገባት አይችሉም።
- በአሁኑ ወቅት (2024-2025) ላይ ተሸላሚ የሆኑ ተሳታፊዎች በመጪው የፕሮግራም ዓመት (2025-2026) ላይ ለማመልከት **ብቁ አይደሉም**።

በዚህ የገንዘብ ድጎማ ተጠቃሚ ለመሆን **የእርስዎ የሥነ ጥበብ ዝግጅት** ብቁ የሚሆነው የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟላ ከሆነ ነው፡-

- የሥነ ጥበብ ዝግጅትዎ መስፈርቱን ከሚያሟሉ የሲያትል ማዕከሎች በአንዱ ላይ ለሕዝብ ከክፍያ ነፃ እና ክፍት ይደረጋል።
- የሥነ ጥበብ ዝግጅትዎ ከ40 እስከ 90 ደቂቃ ርዝመት ይኖረዋል።

## የገንዘብ ድጋፍ

**የሽልማት ገንዘቡን ለሚከተሉት ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡-** ለአርቲስት ክፍያዎች፣ ለማርኬቲንግ እና ማስተዋወቂያ ክፍያዎች፣ ለፕሮጀክት አስተዳደር እና ለሰው ኃይል ወጪዎች፣ ለዕቃ አቅርቦቶች፣ ለመሣሪያ ኪራዮች ወይም ለሌሎች ከዝግጅት ቅንብር ጋር ለተገናኙ ወጪዎች፣ ለሚያስፈልግ ኢንሹራንስ እና እስከ 10% የሚሆነውን ደግሞ ለምግብ ነክ ወጪዎች ሊጠቀሙበት ይችላሉ። በድጋፍ ገንዘብ ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጁ በቅድሚያ ከተፈቀዱ ተጨማሪ ወጪዎች ሊጸድቁ ይችላሉ።

ከዚህ የገንዘብ ድጎማ ፕሮግራም የሚገኝ ገንዘብ ከከተማዋ ሌሎች የገንዘብ ድጎማ ምንጮች ከመጡ ወይም የሲያትል ማዕከል ዝግጅትን (ለምሳሌ ፌስቲቫል፣ የባህል ዝግጅቶች፣ ወዘተ) ለመደገፍ ከቀረበ የድጋፍ ገንዘብ ጋር መቀላቀል አይችሉም። አመልካቾች ከሲያትል ከተማ አስተዳደር ለአንድ ዓይነት ፕሮጀክት/የሥነ ጥበብ ዝግጅት ሁለቴ ድጋፍ እንዲቀበሉ አይፈቀድም።

አመልካቾች ለሚከተሉት የገንዘብ ድጋፍ ደረጃዎች ማመልከት ይችላሉ፡-

- $2,000 ዶላር ሽልማት (በተለምዶ ከ1 እስከ 2 ተዋናዮች) እና $750 የሚያወጡ የተለያዩ የዝግጅት ቅንብር ድጋፎችን ደግሞ ከሲያትል ማዕከል ያቀርባል
- $4,000 ዶላር ሽልማት (በተለምዶ ከ3 እስከ 5 ተዋናዮች) እና $1,360 የሚያወጡ የተለያዩ የዝግጅት ቅንብር ድጋፎችን ደግሞ ከሲያትል ማዕከል ያቀርባል
- $6,000 ዶላር ሽልማት (በተለምዶ ከ3 እስከ 5 ተዋናዮች) እና $1,800 የሚያወጡ የተለያዩ የዝግጅት ቅንብር ድጋፎችን ደግሞ ከሲያትል ማዕከል ያቀርባል

## የመረጃ ክፍለ-ጊዜዎች

ስለ ፕሮግራሙ እና ለእርስዎ ምርጥ የሆነውን ማመልከቻ እንዴት ማስገባት እንደሚችሉ የበለጠ ይወቁ።

**የመረጃ ክፍለ-ጊዜ 1 (ድብልቅ)**
ሐሙስ፣ ግንቦት 22 ቀን 4:00 - 5:20 ፒ.ኤም (ፓሲፊክ)
በአካል፡- ሲያትል ሴንተር አርሞሪ (Seattle Center Armory)፣ ክፍል 301
ምናባዊ፡- ዌብኤክስ (Webex)
እባክዎን ምላሽ ይስጡ

**የመረጃ ክፍለ-ጊዜ 2 (ድብልቅ)**
ሐሙስ፣ ሰኔ 3 ቀን 10:00 - 11:20 ኤ.ኤም (ፓሲፊክ)
በአካል፡- ሲያትል ሴንተር አርሞሪ (Seattle Center Armory)፣ ክፍል 301
ምናባዊ፡- ዌብኤክስ (Webex)
እባክዎን ምላሽ ይስጡ